# የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የንባብ ክበብ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ

ትምህርት ሚኒስቴር
2009 ዓ.ም

[Pick the date]

# ማውጫ


| ይዘት | ገፅ |
|---|---|
| መግቢያ ………………………………………….. | 2 |
| 1. የንባብ ክበብ ምንነትና አስፈላጊነት ……………………… .. | 4 |
| 1.1 የንባብ ክበብ ምንነት ……………………… .. | 4 |
| 1.2 የንባብ ክበብ አስፈላጊነት ……………………… .. | 4 |
| 2. ዓላማ ……………………… .. | 5 |
| 2.1 የንባብ ክበብ አጠቃላይ ዓላማ ……………………… .. | 5 |
| 2.2 የንባብ ክበብ ዝርዝር ዓላማዎች ……………………… .. | 5 |
| 3. የንባብ ክበብ መርሆዎች ……………………… .. | 6 |
| 4. የንባብ ክበብ ዋና ዋና ተግባራት ……………………… .. | 6 |
| 5. የክበቡ አደረጃጀትና አመራር ……………………… .. | 8 |
| 5.1 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ብዛትና ስብጥር ……………………… | 8 |
| 5.2 የክበቡ ስራ አስፈጻሚ አባላት ተግባራትና ኃላፊነቶች ……………… | 9 |
| 5.2.1 የክበቡ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት …………………………….. | 9 |
| 5.2.2 የክበቡ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት …………………………….. | 10 |
| 5.2.3 የክበቡ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት ……………………………... | 10 |
| 5.2.4 የክበቡ የተማሪ ተወካዮች ተግባርና ኃላፊነት …………………………. | 11 |
| 6. የስብሰባ ጊዜ ………………………………………………. | 11 |
| 6.1 የጠቅላላ አባላት ስብሰባ ……………………………………… | 11 |
| 6.2 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ ……………………………. | 12 |
| 7. የወላጆች፣ የህብረተሰቡና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና ……………… | 12 |

## መግቢያ

ንባብ ከአራቱ መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በተለያየ መልክ የቀረቡ ፣ የሚታዩና ህትመት ላይ የተመሰረቱ መረጃዎችን መረዳት የሚያስችል ክሂል፣ ስልትና ዕውቀት ነው ፡፡ ንባብ ማለት በጣም ሰፊ ትርጉም ያለው የማንበብና የመጻፍ ችሎታ አንድ አካል ነው፡፡ ማንበብ ሲባል ከማንበብ ባሻገር መጻፍን፣ መናገርንና ማዳመጥን አካቶ የሚይዝ ሲሆን የሚነበቡትን ጽሁፎች በአንክሮ ማየትን፣ ተገቢ የሆነ ትንታኔ መስጠትንና የቴክኖሎጂ ክሂል ማዳበርን ያካትታል፡፡ በአጠቃላይ ንበብ ለሚነበበው ጽሁፍ ትኩረት መስጠትን፣ ማስታወስን፣ የቋንቋ ችሎታንና መነቃቃትን የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ሲሆን አእምሯዊ ተግባሮችን አቀናጅቶ የያዘ ክሂል ነው፡፡

ንባብ ማንኛውንም ትምህርት ለመማር መሠረት ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አንደኛ እርከን ላይ ማንበብ የቻሉ ተማሪዎች ለወደፊቱ የትምህርት እና የህይወት ስኬታቸው አይነተኛ ሚና እንዳለው የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ዛሬ በአለማችን ላይ ከ250 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የታዳጊ ሀገራት ህፃናት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቆይታ ውስጥ መሠረታዊ ቃላትን የማንበብ ችግር እንዳለባቸው የዩኔስኮ ጥናት ያመለክታል። ከልጅነታቸው ጀምሮ ማንበብን በአግባቡ ያልቻሉ ተማሪዎች በቀጣይ የትምህርት እርከኖች የተወሣሠበ ችግር ይገጥማቸዋል። በተጨማሪም ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለመረዳት ያላቸው ክህሎት በጣም ዝቅተኛ ይሆናል። አንዳንዶቹም ይህንን ማድረግ ባለመቻላቸው ትምህርታቸውን የሚያቋርጡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

እ.ኤ.አ በ2010 በሀገራችን በስምንት ክልሎች በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ላይ የተካሄደ የንባብ ክሂል ግምገማ (Early Grade Reading Assessment) ውጤት እንደሚያሳየው ጥናቱ በተደረገባቸው ክልሎች ከሚገኙ የ2ኛ እና የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት ህጻናት አንብበው መረዳት የማይችሉ መሆናቸው ተረጋግጧል። በተጨማሪም አብዛኛዎቹ ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እየተማሩ ቢሆንም አጥጋቢ በሚባል ደረጃ መጻፍ የማይችሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዘርፉ ባለሙያዎች በተገቢው ሁኔታ ማንበብና መጻፍ ለተሻለ የትምህርት ውጤትና የህይወት ስኬት ወሳኝ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም የንባብ ብቃት ከትምህርት ውጤት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይም ሌሎች ጥናቶች እንደሚያሳዩት በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ተማሪዎች ባሉባቸው የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ክፍተቶች ምክንያት አጠቃላይ የትምህርት ውጤታቸው ሊጎዳ እንደሚችል ያመላክታሉ፡፡

ሕጻናት በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አንደኛ እርከንም ሆነ በቀጣይ የትምህርት ደረጃዎች በተሻለ ደረጃ ማንበብ እንዲችሉና የንባብ ችሎታቸው በየጊዜው እየዳበረ እንዲሄድ ሰፊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ተማሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እያሉ በክፍል ውስጥ ከሚማሩት ንባብ በተጨማሪ በንባብ ክበባት በመታቀፍ በልዩ ልዩ መንገዶች ማለትም በግል-ንባብ፣ በቡድን ንባብ፣ በጽሞና ንባብና በድምጽ ንባብ ብቃታቸውን የሚያዳብሩበት ሁኔታ መፍጠር ይጠበቃል፡፡

በሀገራችን የህብረተሰቡ የንባብ ባህል ገና ያላደገ በመሆኑ በቅድመ-መደበኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ላይ ባሉ ተማሪዎች የንባብ ባህል ላይም ራሱን የቻለ ተፅእኖ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የንባብ ባህልን ማጠናከርና ማስፋፋት የሚያስችሉ ስልቶችን መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ንባብን ባህል ያደረገ ትውልድ ለመፍጠር እና የንባብ ባህልን ለማሳደግ እንዲቻል የተለያዩ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን በመፍጠር መተግበር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የንባብ ባህል በማሳደግ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ለማሻሻልና በትምህርት እና በህይወታቸው ስኬታማ ሆነው የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት እንዲችሉና ንባብ አፍቃሪ ዜጎች እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያግዝ የንባብ ክበብ አደረጃጀት እና አሰራር መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1. የንባብ ክበብ ምንነትና አስፈላጊነት

### 1.1 የንባብ ክበብ ምንነት

የንባብ ክበብ ተማሪዎችና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ መጻሕፍትንና ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በማንበብ የእውቀት አድማሳቸውን የሚያሰፉበት፣ ስላነበቧቸው፣ ስለሚያነቡዋቸው መጻሕፍትና ልዩ ልዩ የህትመት ውጤቶች የሚወያዩበትና ሀሳብ የሚለዋወጡበት እንዲሁም ልዩ ልዩ መጽሀፍትን የማግኘትና የማንበብ ዕድል የሚያገኙበት መድረክ ነው፡፡ በመሆኑም የንባብ ክበብ ማለት ተማሪዎች በተወሰኑ ጊዜያት በመደበኛነት እየተገናኙ ስላነበቧቸው መጻሕፍት ዕወቀት የሚቀስሙበት እና የሚወያዩበት እና የንባብ ክበብ አባላት ያሏቸውን መጻሕፍት አሰባስበው የሚዋዋሱበት አደረጃጀት ነው፡፡

የንባብ ክበብ ተማሪዎችን ከልጅነታቸው ጀምሮ የንበብ ፍቅርና ልምድ ይዘው እንዲያድጉ የሚያስችል አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች እንደየእድሜ ደረጃቸው ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ ስለሀገራቸውም ሆነ ስለ አለምአቀፋዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች  መረጃ የሚያገኙበት የመማማሪያ ስልት ነው።

### 1.2 የንባብ ክበብ አስፈላጊነት

የንባብ ክበብ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት  በማሳደግ የማንበብ  ብቃታቸውን  ለማሻሻል የሚያግዝ ሲሆን በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የንባብ ባሕልን ከህጻንነት ጀምሮ መሠረት ለማስያዝ የሚያስችል መንገድ ነው፡፡ የንባብ ክበብ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ጉልህ ድርሻ ያለው ከመሆኑም በላይ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በጠቃሚ ጉዳዮች ላይ እንዲያሳልፉ  አስተዋጽኦው የላቀ  ነው፡፡

በመሆኑም ፡-

- የንባብ ባህልን በት/ቤትና ከት/ቤት ውጪ ባለው ማህበረሰብ ለማስፋፋት ስለሚያስችል፤
- የተማሪዎችና አጠቃላይ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የንባብ ፍላጎት ለማርካት ስለሚረዳ፤
- የተማሪዎችንና የት/ቤቱን ማህበረሰብ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ መጻህፍት ለማቅረብ ስለሚያሰችል፤

- ❖ ተማሪዎች የተለያዩ መጻህፍትን በማንበብ እርስ በርስ የመማማር ልምድና ችሎታቸውን ለማጎልበት ስለሚረዳ፤
- ❖ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነቶች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዝግቡ ስለሚያግዝ፤
- ❖ ተማሪዎችና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ወቅታዊነት ያላቸው አካባቢያዊና አለምአቀፋዊ ክስተቶችን እንዲገነዘቡ ስለሚረዳ፤
- ❖ በትምህርት ቤቶች የንባብና የስነጽሁፍ ውድድሮችን በማካሄድ በተለያዩ ዘርፎች የተማሪዎችን ክህሎትና ችሎታ ስለሚያዳብር፤
- ❖ ንባብን ለማስተማር ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር፤
- ❖ ተማሪዎች እየተዝናኑ ዕውቀት የሚጨብጡበትን ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር፤
- ❖ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያገኙት በተጨማሪ የማንበብ ዕድል ስለሚሰጥ የንባብ ክበባትን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. ዓላማ

### 2.1 የንባብ ክበብ አጠቃላይ ዓላማ

የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የንባብ ባህልን በማዳበር የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎትና ችሎታ በማሳደግ በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ እና የስነ-ጽሁፍና የፈጠራ ችሎታ ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችል መሰረት ለመጣል ነው፡፡

### 2.2 የንባብ ክበብ ዝርዝር ዓላማዎች

- የንባብ ፍላጎትንና ክህሎትን ለማሳደግ፣
- በግልም ሆነ በቡድን የንባብ መድረክ ለመፍጠር፣
- መጻህፍትን በማንበብ ሀሳብ የሚጋሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣
- በክፍል ውስጥ ያገኙትን ትምህርት ለማዳበር፣
- የተማሪዎችን በራስ መተማመን ለማጠናከር፣
- በመተጋገዝ መማማርን ለማመቻቸት፣
- በንባብ ዕውቀትንና አወንታዊ አመለካከትን ለማዳበር፣
- ለማንበብ የሚቸገሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ፣
- መጻሕፍትን የማሰባሰብ፣ የመዋዋስና የማንበብ ዕድልን ለመፍጠር፣

- በአንባቢዎች መካከል የንባብ ልምድን ለመለዋወጥ

## 3. የንባብ ክበብ መርሆዎች

ይህ የንባብ ክበብ መመሪያ የሚከተሉት መርሆዎች አሉት።

- ማንኛውም ፍላጎት ያለው/ያላት ተማሪ እና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ልዩነት ሳይደረግበት የንባብ ክበቡ አባል መሆን ይችላል/ ትችላለች፡፡
- በንባብ ክበቡ ለንባብና ለውይይት የሚመረጡ መጻህፍትና ርዕሰ-ጉዳዮች መልካም ስነምግባርን ሊገነቡ የሚችሉና የተማሪዎችን የመረዳት አቅም ያገናዘቡ መሆን ይገባቸዋል፡፡
- የክበቡ አባላት ሀሳባቸውን በነፃነት የማቅረብ መብት አላቸው።
- ሁሉም የክበቡ አባላት የክበቡን መተዳደሪያ ደንብ ማክበር አለባቸው፡፡
- የክበቡ አባላት በስብሰባዎች ላይ መገኘትና ሀሳብ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በህዝቦች መካከል መለያየትን የሚፈጥሩ፣ አጓጉል ልማዶችን የሚያንፀባርቁ፣ ከህዝቡ ባህልና ሀይማኖት ተጻራሪ አስተምህሮ ያላቸው፣የስርዓተ-ጾታ ጉዳዮችን ያላማከሉ፣ በአካል ጉዳተኞችና አካልጉዳተኞች መካከል ልዩነትን የማያንጸባርቁ መጻህፍት በክበባቱ ውስጥ ለንባብ መቅረብ የለባቸውም፡፡
- በውይይት ጊዜ ከውይይቱ ጭብጥ ውጪ በመውጣት አላስፈላጊ አርዕስቶችን /ለክበቡ ህብረትና አላማ የማይጠቅሙ / በማንሳት ጊዜ ማባከን የለባቸውም።
- የሚደረጉ ውይይቶች ክበቡ የተቋቋመበትን ዓላማና ተግባር መሰረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 4. የንባብ ክበብ ዋና ዋና ተግባራት

የንባብ ክበቡ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት አሉት።

- የክበቡን አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት፣ ክትትል ማድረግና ግብረ መልስ በየጊዜው መስጠትና የተሰሩ ተግባራትን ሪፖርት በመገምገም ለትምህርት ቤቱ ማቅረብ፤
- የንባብ ልምድና ግንዛቤን ሊያሳድጉ የሚችሉ የተለያዩ መድረኮች በመፍጠር የትምህርት ቤቱን ተማሪዎችና ማህበረሰብ ለንባብ ማነሳሳት፤

- ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በመመካከርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የተለያዩ ገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመቀየስ የክበቡን የፋይናንስና የማቴሪያል ምንጮችን ማጎልበት፤
- ራሱን የቻለ የማንበቢያ ክፍልና ቁሳቁሶችን ማሟላትና ማደራጀት፤
- የክበቡን አላማና ተግባር ሊያስተዋውቁ የሚችሉ የተለያዩ በራሪ ጽሁፎችን፣ ፖስተሮችንና ሌሎች መጽሄቶችን በማዘጋጀት የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በንባብ ጠቀሜታ ላይ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፤
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ቤተመፃሕፍት እንዲጠቀሙ መቀስቀስ፡፡
- በሳምንት የንባብ ቀን እንዲሁም በአመት የንባብ ሳምንት መቼ መሆን እንዳለበት መወሰንና የሚከናወኑ ተግባራትን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፤
- በንባብ ቀን የትምህርት ቤቱን ሚኒ ሚዲያ በመጠቀም በትምህርታቸውም ሆነ በስነምግባራቸው አርአያ የሆኑ ተማሪዎች እና ታዋቂ ግለሰቦችን በመጋበዝ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ማነሳሳት፤ እንዲሁም በትምህርት ቤት በሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓትና በልዩ ልዩ የት/ቤት ስብሰባዎች ወቅት ተማሪዎች አጫጭር ጽሑፎችን የሚያነቡበት መድረክ ማዘጋጀት፣
- ሴት ተማሪዎች፣ የልዩ ፍላጎት ያላቸው፣ አካል ጉዳተኞችና የማንበብ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በንባብ ክበብ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ትኩረት መስጠት፤
- የንባብ ክሂል ውድድርን በትምህርት ቤት ውስጥ በማካሄድ በተማሪዎች መካከል የውድድር ስሜት በመፍጠር የማበረታቻ ሽልማት መስጠት፤
- ምርጥ የንባብ ተሞክሮዎችን ማሰባሰብ እና ከሌሎች አቻ ትምህርት ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፤
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በፍላጎታቸው የክበቡ አባል እንዲሆኑ ቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፤
- የንባብ ክሂልና ችሎታን ለማሻሻል ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የተቀናጀ ስራ መስራት፤
- ለክበቡ መጠናከር ፍላጎት ያላቸውን ተባባሪ አካላት በመለየት እና በመመዝገብ አስተጻዋጾኦ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤

- ከትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጭ ለንባብ የሚያመች ጊዜና ቦታ እንዲዘጋጅ እንዲሁም በየክፍሉ የንባብ ጥጎች እንዲኖሩና የመጽሐፍ ውሰት ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የክፍል ደረጃ፣ ዕድሜ ፣ ባህል ፣ ቋንቋንና የአካባቢ ሁኔታን የሚመጥኑ የንባብ መጻሕፍት እና ሌሎች ሕትመቶች እንዲኖሩ ከት/ቤቱ ጋር አብሮ መሥራት፣
- በት/ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ልዩ ክበባት ጋር በመቀናጀትና በመተባበር መሰራት፤
- በጉድኝት ማዕከላት ስር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውድድር እና ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማመቻቸት ።

በዚህ መሰረት የትምህርት ቤት የንባብ ክበብ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ተግባራት እንዳስፈላጊነቱ ሊያከናውን ይችላል፡፡ ተግባራቱ ለንባብ ክበቡ ዓላማዎች መሳካት አስተዋጽኦ ማድረግ እስከቻሉ ድረስ በየጊዜው እየተሻሻሉና እያደጉ እንዲሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 5. የክበቡ አደረጃጀትና አመራር

በትምህርት ቤት የንባብ ክበብ የሚቋቋመው ፍላጎት ባላቸው በትምህርት ቤቱ ተማሪዎችና ሌሎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት ሲሆን የአባላቱ ቁጥርና ስብጥር እንደ ትምህርት ቤቱ ስፋትና ጥበት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል። ክበቡን የሚመራ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይደራጃል፡፡ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከአስተዳደር ሰራተኞች የሚመረጡ ይሆናል፡፡ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ይሆናል፡፡

### 5.1 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ብዛትና ስብጥር

የክበቡ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ሆኖ የአባላት ብዛትና ስብጥር ከዚህ በታች እንደተቀመጠው ይሆናል። ይሁን እንጂ በአደረጃጀት ምክንያት ምክትል ርዕሰ መምህር የሌላቸው ትምህርት ቤቶች የክበቡ የስራ አስፈጻሚ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ይሆናል፡፡

- የቋንቋ መምህር--------------- ብዛት 1 (ሰብሳቢ)

- ከመምህራን ተወካይ ------ ብዛት 1(ጸሀፊ)
- ከቤተመፃህፍት ባለሙያ--- ብዛት 1(የገንዘብ ያዥ) (የቤተመፃህፍት ባለሙያ ባልተመደበበት ተወካዩ አባል ሆኖ ይሰራል)
- ከተማሪዎች ተወካይ ----- ብዛት 4 (አባላት)

## 5.2 የክበቡ ስራ አስፈጻሚ አባላት ተግባራትና ኃላፊነቶች

### 5.2.1 የክበቡ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

የክበቡ ሰብሳቢ ተጠሪነቱ/ቷ ለክበቡ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል/ታከናውናለች፡፡

- አጀንዳ በማዘጋጀት የክበቡን ጠቅላላ ጉባኤና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባ መጥራትና መምራት፤ እንደአሰፈላጊነቱም አሰቸኳይ ስብሰባ መጥራት፤
- የክበቡን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በማዘጋጀት ማጸደቅና ሥራ ላይ ማዋል፤
- የክበቡን ዕቅድ ዝግጅት ማስተባበርና የተዘጋጀውን እቅድ ከሌሎች የክበቡ አባላት ጋር በመሆን መገምገምና ማፀደቅ፤
- ክበቡን በበላይነት መምራት፤
- የክበቡን ዓላማዎችና ተግባራት መፈጸምና ማስፈጸም፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ክበቡ የሚጠናከርበትን መንገድ ማመቻቸት፤
- የክበቡን የቅስቀሳና የማስተዋወቅ ተግባር በበላይነት መምራት፤
- ክበቡ የተቋቋመበትን አላማ እንዲያሳካ ከሌሎች ክበባት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- የአባላት ቁጥር የሚጨምርበትን መንገድ መቀየስ፤
- ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርና ምክትል ርዕሰ መምህር በሚያገኘው ዕውቅና መሰረት ከሌሎች ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር የስራ ግንኙነት ማድረግ፤
- ክበቡ በገንዘብና ቁሳቁስ ራሱን የሚችልበት ስልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፤
- የንባብ ሳምንት የሚከበርበትን ቀን ከትምህርት ቤቱ አመራሮች ጋር በመሆን መወሰን፤
- የክበቡ አባላት ልምድ መቅሰም የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
- ውጤታማ አንባቢዎችን በመከታተል ማበረታታትና እውቅና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

- በትምህርት ቤት ደረጃ የንባብ ቀን በሳምንት ቢያንስ 1 ቀን ከ1-2 ሰዓት እንደ ተማሪዎቹ ምርጫና የክፍል ደረጃ የሚወሰን ሆኖ የሚከበርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- አዳዲስ አሰራሮችንና የፈጠራ ችሎታን ለማዳበር ሀሳብ በማመንጨትና ባለሙያዎችን በማስተባበር ለእርስ በርስ መማማር አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
- የክበቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በመከታተል የወር፣የ3 ወር ፣ የ6ወር፣ የ9 ወርና የዓመት ክንውን በመገምገም ሪፖርት ማቅረብ፤
- እንደ አሰፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ለምሳሌ የመጻሕፍት አሰባሳቢ፣ የገቢ ማስገኛ ወዘተ…ማቋቋም፣ መከታተልና መደገፍ፤
- የአካባቢውን ህብረተሰብ በማስተባበር የንባብ ባህል እንዲዳብር ልዩ ልዩ ስልቶችን ቀይሶ መስራት፤
- ለክበቡ መጠናከር የሚያግዙ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፤

### 5.2.2 የክበቡ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

- ሰብሳቢው በሌለበት ጊዜ ክበቡን መምራት፤
- የስብሰባ ቃለጉባኤዎችን መያዝ፤
- አባላትን መመዝገብና መረጃ መያዝ፤
- የክበቡን ልዩ ልዩ ሰነዶች በአግባቡ መያዝ፤
- የክበቡን አመታዊ እቅድ ከአባላት ጋር በመሆን በዝርዝር ማዘጋጀትና ማጸደቅ፤
- የተከናወኑ ተግባራትን በአባላት እንዲገመገሙ ማድረግ፣ ሪፖርቶችና ማዘጋጀት፤
- ልዩ ልዩ የንባብ ውድድር መድረኮችን ማመቻቸት፤
- የክበቡን የፋይናንስና የቁሳቁስ አቅም ለማጎልበት የሚያግዙ ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፤
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ የንባብ ባህል እንዲያድግ ልዩ ልዩ ስልቶችን ቀይሶ መስራት፤
- ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን፤

### 5.2.3 የክበቡ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

- የፋይናንስ ደንብና መመሪያን መሰረት ባደረገ መልኩ የንባብ ክበቡ ገንዘብ ያዥ ሆኖ ማገልገልና አስፈላጊ ክፍያዎችን መፈጸም፤

- ከኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን ልዩ ልዩ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፡፡ ለምሳሌ ምንጩ አነስተኛ የተማሪዎች መዋጮ፣ ልዩ ልዩ ድራማዎችን ማሳየት፣ ባዛር ማዘጋጀት፣ ከወላጆችና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ድጋፍ ማሰባሰብ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፤
- የክበቡን የፋይናንስ ሰነዶችን በአግባቡ ማደራጀት መያዝና መከታተል፤
- የክበቡን ንብረቶች በአግባቡ መያዝ፤
- የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዕቅድ አውጥቶ በማፀደቅ መተግበር፤
- ስለክበቡ ገንዘብና ሌላ ሀብት ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ለክበቡ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሪፖርት ማቅረብ፤
- ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን፤

### 5.2.4 የክበቡ የተማሪ ተወካዮች ተግባርና ኃላፊነት

- በትምህርት ቤቱ ያሉ ሌሎች ክበባት በሚያዘጋጁቸው ፕሮግራሞች የንባብ ባህልን አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት፤
- ንባብን ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ህትመቶችን ማሰባሰብና ማሰራጨት፤
- የክበቡ አባላት ባነበቧቸውና በሚያነቧቸው መጻሕፍት ዙሪያ የውይይት መድረኮችን መምራት፤
- ከቤተ-መጻህፍቱ ጋር በመቀናጀት አዳዲስ የወጡና ነባር ህትመቶችን እየመረጡ በአባላት እንዲነበቡ ማድረግ፤
- የንባብ ውድድር ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ እንዲከናወን መቀስቀስና ማስተባበር፡፡
- ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን፤

## 6. የስብሰባ ጊዜ

### 6.1 የጠቅላላ አባላት ስብሰባ

በየሩብ ዓመቱ የሚከናወን ሆኖ መስከረም ወር ላይ በክበቡ አመታዊ ዕቅድ ላይ የሚወያይ የጠቅላላ አባላት ስብሰባ ይካሄዳል፡፡ በሰኔ ወር መጨረሻ ላይ በክበቡ አመታዊ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ የሚወያይ የጠቅላላ አባላት ስብሰባ ጉባኤ ይካሄዳል፡፡

## 6.2 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ በየወሩ ወር በገባ በመጀመሪያ ሳምንት የሚካሄድ ሆኖ የክበቡን ወርሃዊ የስራ እንቅስቃሴ እየገመገመ የማስተካከያ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፡፡

## 7. የወላጆች፣ የህብረተሰቡና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና

ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲሁም ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ራሳቸውን በማብቃት ለማህበረሰቡ ዕድገት ማበርከት ያለባቸውን ድርሻ ለመወጣት እንዲችሉ ወቅቱ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ማህበራዊና ሳይንሳዊ ዕውቀት እንደዚሁም ተግባራዊ ልምምድ ላይ የተመሰረተ ክሂል የሚጨብጡበትን ሁኔታ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ የሁሉም የማህበረሰብ ሀላፊነት ነው።

ባጠቃላይ ወላጆች፣ ህብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት:-

- የክበቡን ቁሳዊ ችግሮችን በማቃለል
- የክበቡ አባላት የሚያጋጥሟቸው ችግሮችን በመፍታትና በክበቡ የሚከናወኑ ተግባራትን በመደገፍ
- ያላቸውን ዕውቀት፣ ልምድና ሙያ ለክበቡ አባላት በማካፈል
- ከትምህርት ቤት ውጪ የሚገኙ ከንባብ ተግባራት ጋር አግባብነት ያላቸው አገልግሎችን እንዲጎበኟቸውና እንዲገለገሉባቸው በመፍቀድ ድርሻቸውን ለወጡ ይገባል።